# ለአማርኛ ተናጋሪዎች
# የቋንቋ መሰናክሎችን ማስወገድ

በአፍሪካ ትራንስሌሽን የተዘጋጀ

# ቋንቋ ክቡር ነው

- አማርኛ ተናጋሪው ሕብረተሰብ እንግሊዘኛ አውቃለሁ ቢልም አንድ ለንግድ የቆመ ድርጅትም ሆነ የመንግስት አካል መረጃዎቹን እና ግልጋሎቶቹን በአማርኛ የሚያቀርበው ለሕብረተሰቡ ያለውን ክብር ለማሳየት፤ ሕግን ለማክበር፤ እናም ምርቶቹን እና ግልጋሎቶቹን በይበልጥ ለማስተዋወቅ ነው፤፤

# መብትዎን ይወቁ!

- መንግስት መስሪያ ቤት፣ ፍርድ ቤት ወይም የጤና ድርጅቶች ነፃ ባለሙያ አስተርጓሚ እንዲያቀርብልዎት ይጠይቁ፡፡
- ቋንቋ ክቡር ነው፣ መጠየቅ መብትዎ ነው፣ እስካልጠየቁ መብትዎንም ሆነ ራስዎን አላከበሩም፡፡

- አስተርጓሚ ልክ እንደ አንድ ስልክ መግባቢያ መሳሪያ ነው
- ስልክ ሩቅ ያለ ሰውን ለማናገር እንደሚያስችልዎት ሁሉ አስተርጓሚ ደግሞ ሌላ ቋንቋ የሚናገር ሰው እንዲያናግሩ ያስችለዎታል
- ሩቅ ካለ ሰው ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ የስልክ መስመሩ ችግር ኖሮት የሚናገሩትን አጉድሎ ለእርስዎ የሚባለውን ቀንሶ ከሆነ የሚያገናኝዎ ይህ ስልክ አይጠቅመኝም ብለው ሌላ ስልክ ያስፈልገኛል እንደሚሉት ሁሉ ጉዳይ ለማስፈጸም ቀርበው የሚጠቀሙት አስተርጓሚ ልክ እንደተበላሸ የስልክ መስመር የሚሉትን ቀንሶ ለእርስዎ የሚባለውን አጉድሎ ከሆነ የሚተረጉመው ይህ አስተርጓሚ ይቀየርልኝ ማለት የእርስዎ መብት ነው
- እርስዎ ሩቅ ካለ ሰው ጋር ሲነጋገሩ የሚንጫጫ የስልክ መስመር መጠቀም አንደማይፈልጉ ሁሉ ሌላ ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ያልተባለውን ጨምሮ የተባለውን ቀንሶ ላስተርጉምልዎ የሚለውትን አሻፈረኝ ማለት መብትዎ ነው

- መብትዎ ለእርስዎ ሊሰራ የሚችለው፤ መብትዎን ሲያውቁ እና እርስዎ ባለቤቱ ሲያስከብሩት ብቻ ነው

- የቀረበልዎ አስተርጓሚ ብቃት ያንስዋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ወይም አስተርጓሚ የሚለውን ካልተረዱ አስተርጓሚ የሚለውን አልተረዳሁም ሌላ አስተርጓሚ ይመደብልኝ ብሎ የመናገር መብት የእርስዎ ነው

- እንግሊዘኛ ቋንቋ እችላለሁ ከማለትዎ በፊት የሚከተሉት ጥያቄዎች ራስዎን ይጠይቁ

- ግለሰቦችን፤ ቦታዎችን፤ ሁኔታዎችን፤ ክስተቶችን በትክክል በእንግሊዘኛ መግለጽ እችላለሁን?
- በምን ጊዜ ምን እና እንዴት እንደተከናወነ በብቃት በእንግሊዘኛ ማብራራት እችላለሁን?
- በጥያቄ ጊዜ ሐሳቤን ውድቅ ለማድረግ የሚሰነዘሩ አስተያየቶችን መረዳት በእንግሊዘኛ እችላለሁን?
- አቋሜን ማስጠበቅ እና መከላከል በእንግሊዘኛ እችላለሁን?

- ለማናቸውም ለነዚህ ጥያቄዎች መልስዎ አልችልም ከሆነ የምናገረው አማርኛ ነው፤ እንግሊዘኛ አልችልም ፤ ወይም የእንግሊዘኛ ችሎታዬ ውስን ነው፤አስተርጓሚ ያስፈልገኛል ይበሉ